# ይሁዳም ስለ ድሆች ሞግተዋል!

የትኛውም ቤተ-እምነት ትከታይ ይሁን ኢትዮጵያዊ ሆኖ በኢትዮጵያ ምድር ተወልዶና አድጎ ሌላው ይቅር ይሁዳ የሚል ስም የማያውቅ አለ ለማለት እጅግ ይከብዳል። በዛሬው ርዕሳችን አንስተን የምንወያየው ይሁዳ ሀገር፣ የያዕቆብ ልጅ፣ የደማስቆውም ይሁዳ ሳይሆን የአስቆሮቱ ይሁዳ ይሆናል (ማቴ. 10፥4)። የሀገሬ ሰው ትልቁም ትንሹም እምነቱ ላጎደለ፣ ለሳተና ላጠፋም ቢሆን ከሚሰጣቸው ስሞች መካከል አንዱ ይህን ነው ይሁዳ የሚል። ይሁዳ ማለት ያልተማረ ምንም የማያውቅ ደንቆሮ ማለት አይደለም። ይሁዳ ማንም ያላገኘውን ዕድል አግኝቶ ማለት ከተቀሩት 11 የጌታ ሐዋሪያት እኩል ለሦስት ዓመታት ያክል ከእግዚአብሔር ልጅ ከጌታ. ከመድ. ከኢየሱስ ክርስቶስ ባደረበት እያደረ በዋለበት እየዋለ ከአፉ ያፈርስና ይተክል ዘንድ ሐይል ያለው፣ ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ፣ ደንዳና ልብን እንደ መዶሻ መትቶ የሚያፈርስ እንደ እሳትም ቆሻሻን የሚበላ ቃል የተማረ ሰው ለመሆኑ ምንም አያጠያይቅም። በግርድፉ ይሁዳ ማለት የተማረ የተመራመረ ሰው **ነበር**።

ይሁዳ ሥሙ ያማረ (የስሙ ትርጓሜ "ማመስገን" ከሚል ግሥ የተመሰረ ሲሆን ምሥጋና ማለት ነው) ሰው የማያውቀው ልብና ኩላሊትን የሚመረምር ጌታ የገለጠው ድብቅ ተግባሩና ማንነቱ ግን ፍጹም የተለየና እውነትም ነፈሰ-ገዳይ ዓይነት ሰው ነበር። ይሁዳ ቀን እስኪለይ (ዘመን እስኪ መጣ) ድረስ እኩል ከሌሎች ደቀ-መዛሙርት ጋር ይጓዝ የነበረና ጉባኤው ትልቅ ሃላፊነት የጣለበት ሰውም ነበር። ይሁዳ የሂሳብ (የቁጥር) ሰው/ሊቅ ሳይሆን አይቀርም ይላሉ የሥነ-መለኮት መምህራን። ለዚህ አባባላቸውም እንደ አንድ ጭብጥ አድርገው የሚያቀርቡት በጉባኤው (በክርስቶስ ኢየሱስ አገልግሎት) የሂሳብ ሹም ሆኖ መሾሙ ነው ያላሉ። እውነት ነው ይሁዳ ማለት የሐዋርያት ገንዘብ ያዥ ነበር። ይሁዳ ልቡ በሚያውቀው በተደጋጋሚ ጌታ ያስጠነቀቀው ሲሆን አንድ ጊዜ ገንዘብ ማለት እንዴትና ምን ምን እንደሚጥምም ስለ ገባው ግን የጌታን ግሳጼ ልብ ባለማለቱ ጭራሽ ሰይጣን ገብቶበት የቀረበት ሂሳብ ለማካካስ ጌታውን ለመሸጥ የበቃም ነው (ማቴ. 26፥20-25, ዮሐ. 13፥2, 21-30 ይመልከቱ)።

ይሁዳ የልቡን በልቡ ቋጥሮ ከሌሎች ይልቅ እሱ ብቻ ስለ ድሆች እንደሚያስብና እንደሚቆረቆር "እንዴ! ሰዎች የሚላስ የሚቀስም አጥተው በርሃብ አለንጋ ሲገረፉ ይቺ ደግሞ ይህን 300 ዲናር የሚያወጣ የከበረ ሽቶ ሰብራ እግሩ ላይ ትደፋዋለች እንዴ?" ብሎ/እያለ ሲሞግት እንግዲህ እርስዎ የዋኅ ካለሆኑ በስተቀር "እውነት ነው! ሽቶው ተሸጦ ጧሪ ቀባሪ ለሌላቸው አረጋውያን፣ ያለ አሳዳጊ ለሚንከራተቱ ህጻናት እርዳታ መዋል ይገባው ነበር" በማለት ድምጽዎትን ለይሁዳ ይሰጡ ይሆን? እንግዲህ መጽሐፍ ይሁዳ "ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበረ ነው።" (ዮሐ. 12፥6) ሲል መጽሐፍ ምን ይሰማዎታል?

ጻዲቁ የእግዚአብሔር ሰው ኢዮብ "ነፍሰ ገዳዩም ሳይነጋ ማልዶ ይነሣል ችግረኞችንና ድሆችን ይገድላል፤ በሌሊትም እንደ ሌባ ነው።" (ኢዮ. 24፥14) ሲል እንደሚናገረው ይሁዳዎች በየትኛውም ስፍራ/ቦታ በማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ እውነተኞች መስለው ለመቅረብና ለመሟገትም ማንም አይቀድማቸውም። ይሁዳዎች ትጉዎች ይባሉና ይመስሉም ዘንድ በማለዳ ከሰው ይልቅ ቀድመው የሚነሱና የሚገሰግሱም ናቸ<u>ው</u> (ልዩ ምልክቱ ጠብቆ ይነበብ ዘንድ ነው)። በሌሊትም በቀን መልካሞች፣ ተሟኞች መስለው ለመታየትና እንደሚቀርቡ ሳይሆን ሌላ ምስል ነው ያላቸ<u>ው</u> ሌቦች፣ ነፍሰ-ገዳዮችና በሀገርና በሕዝብ ሥም የሚነግዱ አመንዝሮች ናቸው ሲል ለብዙሐኖቻችን በግልጽ የማይታይና ያልታየ እውነተኛ ካራክተራቸው/ ገጽታቸው የሚነግረን።

በድጋሜ ጠቢቡ ስለ የሌባ ዓይነት የሚለው-አለው "ሌባ በተራብ ጊዜ ነፍሱን ሊያጠግብ ቢሰርቅ ሰዎች አይንቁትም" (ምሳ. 6፥30) እንዲል በሌላ አገላለጽ ይህ ቃል የሌብነት ዓይነት እንዳለውና ይህን ዓይነቱ ከጥጋብ የተነሳ ሌብነት ሳይሆን ጣመኝ ድገመን እየተባለ እጅ ብቻ ሳይሆን ሁለመና የሚነክር ሌብነት/ ይሁዲነት እንዳለ ለማስየት ነው። እንዴት? ቀጥለን በስፋት የምናየው ይሆናል። ጠቢቡ ልማድ ሆኖት ሳይሆን አንድ ሰው ከችግር የተነሳ ሰርቆ ሆዱን ቢያስታግስ፣ ቢመግብና ነፍሱን ቢያተፍ ሰዎች የድርጊቱን መንስኤ ሲለሚረዱ መራብ ማለት ምን ማለትም እንደሆነ የርሃብ አስከፊነት በደንብ ስለሚገባቸው በእንዲህ ዓይነት ሰው ላይ ሰዎች ለመፍረድም ሆነ ድንጋይ አንስተው ወግረው ለመግደል አይቸኩሉም። እንደ ምንጭ ውሃ ጣፍጦት እግር እየጠበቀ የሰውን ሚስት ለሚይልግ ለእሱ ግን ቅጣትን ይገባዋል ይሆናል በላይም በታች ቤትም ፍቹ።

እንግዲህ ወደ ነባራዊው የሀገራችን ሁኔታ ስንመጣ ታድያ ሌባ/ይሁዳ ማን ነው? በእያለንበት ሆነን ገዢው የኢህአዴግ መንግሥትም ሆነ ከእሱ በማይተናነስ መልኩ ምድሪትዋንና የኢትዮጵያ ሕዝብ እየበደሉና እያስለቀሱ ያሉትንና የሚገኙትን ግለሰቦችም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች "ሲቸግራቸው ነው" ብለን አላለፍነውም ድርጊታቸውን ቢሆን ከማውገዝ አላረፍንም። በተገኘ አጋጣሚ ሁሉ ስለ ኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ የግፍና የሰቆቃ መዓት ለዓለም የምናስተዋውቀው እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት አቤት የምንለው፣ ድምጻችን ማሰማት የማንተወውና ቅጣት/ፍርድ ይገባዋል/ይገባቸዋል ስንል የምንጮሆው ሌባው ጠቢቡ ከነገረን እና ከሚነግረን ለየት ያለ ቅጣት የሚገባው ሌባ ስለመሆኑ ማንም አይስተውም።

እንግዲህ ዮሐንስ እንዳለው ዘንዶው "ስለ ኢትዮጵያ ነጻነት ቅጠል ምሰን በልተናል፣ ስለዚህ-ህዝብ ሽንታችን ጠጥተን ታግለናል፣ ስለዚች ምድር አንድነት የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ማረጋገጥ ደማችን አፍስሰናል፣ የህይወት መስዋዕትነትም ከፍለናል ..." ሲል እባቡም በፊናው "ሕዝቤ፣ ሀገሬ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ተረገጠ፣ ተጨፈጨፈ፣ (የኢትዮጵያ ህዝብ አለተረገጠም፣ አለልተጨፈጨፈም ግፈኛው የኢህአዴግ መንግሥት 1000 ዓመት ይንገሥ እያልኩ ሐቁን እየካድኩ አበራኛውን የወያኔ መንግሥት እያወደስኩ አይደለም ያለሁት። አላልኩም! አዎ! ከመረገጥም በላይ ከመጨፍጨፍም በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተረግጠዋል፣ ተጨፍጭፈዋል! እየተረገጠም እየተጨፈጨፈም ይገኛል)፣ የህግ የበላይነት የሚባል በምድሪትዋ የለም (አዎ! የለም)፣ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የለም (አዎ! የለም አንባገነን መንግሥት ነው)፣ ..." ይላሉ።

ጥያቄው እውነት ስለ ሕዝባቸው የታገሉ፣ ደማቸውን ያፈሰሱ፣ የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉ ሕዝብን አፍነው፣ ረግጠው፣ አንቀጥቅጠውና ውጠው ለማበጥና ለመግዛት ነው እንዴ? በውኑ ሀገሬ! ሕዝቤ! እየተባለ በሕዝብ ስም ጩሆው የሚያጫጭኹና ጮቤ የሚረግጡትስ ቢሆኑ (ሕዝብ ባያውቃቸውም) ደማቸው ቢመረመር (እግዚአብሔር ቢገልጣቸው) እውነት ሀገራቸውና ሕዝባቸው ግድ ብሎአቸው ይሆን? ሀገሬ ሆይ! ይሁዳም ስለ ድሆች ሞግተዋል! ስለ ድሆች መሞገት በራሱ ኃጢአት ሆኖ ሳይሆን ያስወቀሰው በልቡ ሌባ ስለ ነበር ነውና ስለ ነገ ቢጠየቅ በመልሱ የማይሳሳት እግዚአብሔር ይሁንሽ። በኪነ ጥበቡም ሰው ይስጥሽ እንጂ ሰውስ አልወጣልሽም። ክቡር ዜጋ ሆይ! የሚያብለጨልጭ ሁሉ ወርቅ አይደለም። ጉድ ነው! አንዳንዱ ብረት (ቆርኪ) በእሳት ውስጥ አልፎ እስካላዩት ድረስ ሲታይ ከወርቅም በላይ ነው።

ሀገሬ ሆይ! የሀገር መሪም እንደሆነ ከድምጽም ያለፈ ነውና የተፈተነ ይጣልልሽ! በዕድሜም የሸነገለ፣ በትምህርትም ሰው ለሰው የሚሰጠውን ማዕረግ ያጠናቀቀ፣ ተኩሶም ዒላማውን የማይስት አልልም (ትምህርት መቃወሜ አይደለም ከማንም በላይ የማለት ድፍረቱ ባይኖረኝ ከማንም በማይተናነስ መልኩ በእውቀት አምናለሁ የተማሩ ትላላቆቼም አከብራለሁ) እያልኩ ያለሁተይ ከትምህርትም ከታጋይም በላይ ለሀገሩና ለሕዝቡ ልብ ያለው የተሰጠ የህዝብ ህመም ህመሜ ነው፣ የህዝብ ስብራት ስብራቴ ነው፣ የህዝብ ሀዘን ሀዘኔ ነው የሚል ለማለት ነው። በተረፈ ግን ተምሮ ለመብላት፣ ታግሎም ለጥፋት ከሆነ ትምህርቱም ሆነ ትግሉ ለምንሽ ሀገሬ? ለምንህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ?

ሐዋርያው በገላትያ መልዕክቱ "በብርቱ ይፈልጉአችኋል ለመልካም አይደለም ነገር ግን በብርቱ ትፈልጉአቸው ዘንድ በውጭ ሊያስቀሩአችሁ ይወዳሉ" (ገላ. 4፥17) ሲል እንደተናግረው ላይሆኑን ከሚፈልጉን፣ ላይበጇንም ከምንፈልገው የሚታደግና የሚያተርፍ ከሰውም ሆነ ከፍጥረታት ሁሉ የሚመስለው የሌለ ጅማሬና ፍጻሜ የሌለው እግዚአብሔር ይሁነን። ምን ነው? ቢሉ ለይሁዳ ፍቱን መድኃኒቱ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ነውና!! ጴጥሮስ ቢያውቀው ኖሮማ በቁሙ ይሸልተው ነበር (ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ኃይል ከመቀበሉ በፊትን ስለ ቅናቱ ነው እየተናገርኩ ያለሁትይ) እንዲህ ዓይነቱ የይሁዳ ማንነት ግን ተሸፍኖባቸው ነበር። ኢትዮጵያውያን በገዛ ምድራችን የሀገራችን ነገር የተሸፈነብን ዜጎች ነን።

ሌላው ይቅር አልተጻፈም እንጂ ጌታውን ለመሸጥ ከጉባኤ እየተነጠለ አስሬ ወደ ስምምነቱ ቦታ ሲሄድና ሲመላለስ "አገልግሎት አለኝ፣ አንድ ጽዋ ማኅበር ጠርቶኛል፣ እዚህ ቦታ ላይ ጸበል ረጭቼ መጣሁ …" እያለ ስሄድና ሲመለስም "እግዚአብሔር ይመስገን፣ እንዴት ያለ እሳት የሆነ አገልግሎት ነበረኝ መሰላችሁ … ገና ብዙ ተአምር እንሰራለን" እያለ ይሸነግላቸው እንደነበር ነው የማምነው። በዚች ምድርም (በኢዮትጵያም) ቢሆን የቀን ጉዳይ ብቻ ይሆናል እንጂ ከወያኔ የማያንስ ለግል ክብሩና ጥቅሙ በህዝብ ስም የምድሪትዋ ሀብትና ዘር የበላም ደቂቀ-ይሁዳ አለ። መንገደ ብዙ እግዚአብሔር ትልቅ ነው! አስቀድሞ "ሞትን አትሞትም በምድር ሁሉ ግን ተቅበዥባዥ ትሆናለህ" የሚል ማህተም ግንባሩ ላይ ያትምና ከመካከላቸው (ከይሁዳዎቹ) አንዱን ጥቅሙን እንዲነካ በማድረግ እሱ ደግሞ በተራው ላይበላው እንደ ይሁዳ መጽሐፍ ሰርቶ እውነታውን ይተርክልናል። ዕድሜና ጤና ይስጠን ብቻ እንጂ ሌባ ከሌባነቱ አልፎ ጠበቃ፣ አሌኝታ ሊሆን አይችልም!!

ጌታ. መድ. ኢየሱስ ክርስቶስ "ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም" (ዮሐ. 10፥10) ሲል እንደተናገረው ሊሰርቅ፣ ሊያርድና ሊያጠፋ ከሚመጣ የሚታደግ ለሚታመኑት፣ ግብዝነት በሌለበት እምነት በንጹህ ልብ ስሙንም ለሚጠሩት የሌባና የነፍሰ-ገዳይ የልብ ጣቢያ ጠልፎ የሚሰጥ ለሰው ልጅ መልካምና በጎ ፈቃድ ያለው በሰማያት በብርሃናት ውስጥ የሚኖር እግዚአብሔርና ክቡር ዜጋ ሆይ! እግዚአብሔርን አጥብቀን እንሻው። ለሚታመኑት እግዚአብሔር ከልብ ለሚጠሩት ለይሁዳ/ሌባ አሳልፎ አይሰጥምና። እውነተኛ መሳይ ዳሩ ግን የበግ ለምድ የለበሰ ታጋይ መሳይ አጥፊ ሰው ትርፍ እስካስገኘለት ድረስ ሰውን የሚያክል ክቡር ፍጥረት አጋድሞ ኪሱን ከማደለብ አይመለስም። ስለዚህ ከወያኔ አመንምን ዱላ ለመላቀቅም ሆነ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድና ሃሳብ በላይ ላያችን ሊነግሱብን ከሚያደቡ ለመትረፍ ፊታችንን ወደ እግዚአብሔር እንመልስ። በስምህ የሞገቱ ሁሉ ያንተ ናቸው፣ ይሆኑጎል ማለት አይደለምና።

ሰው የነጻነት መንገድ እግዚአብሔርን ሊያስተምረውና ሊጠቁመው አይችልም። የጥበብ ቤትዋ የእውቀትም መንገድዋ የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። የሰው እውቀት ልክ አለው። ሰው ስለ ነገ ቢጠየቅ የማይጨበጥ (መላምት) ገፋ ቢል ደግሞ መልካም ምኞቱን ነው የሚገልጸው። እግዚአብሔር ሲናገር ግን እውነት ነው። "ለዚህስ ተው! እኛም አናንስም፣ ስለ ራሳችን ነጻነት እኛው እናውቅበታለን" ማለት የእግዚአብሔርን ጣት ትከለክላለችና ዘመነ ሰቆቃችን አናራዝም። በባሌም በቦሌም ማለት ለጊዜው ይመስለን እንደሆነ ነው እንጂ ዘለቄታዊ መፍትሔ በምድሪዋ ላይ አያመጣም።

በቅርቡ አንድ አስተያየት ሰጪ እንዲህ ሲሉ በኢ-ሜይል አድራሻዬ ይጽፉልኛል "የወያኔ መንግሥት ለመጣል አይደልም ከሻዓቢያ ከአልሸባብም እንተባበራለን" ሲሉ ጻፉሉኝ። "እውነት" ነው ሰው ከመሰለው የመተባበር መብቱ የተጠበቀ ነው ባለ ሙሉ መብትም ሲሆን ትብብሩ የሚያመጣው (የሚያስከትለውን) ደግሞ አብሮ መቀበል ይጠበቅበታል። ዳሩ ግን ዛሬ ከአልሸባብን መተባበር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያስተማርከው ትውልድ ነገ ደግሞ በተራው ከአልሸባብ የባሰ ለማንም የማይመልስ አይደለም ኢትዮጵያ ዓለምን  በአንዲት እግርዋ የሚያቆም በተጠረበ ድንጋይ የሚበልት የሞአብ አዳጋ ጣዮችን ትፈለፍላህ ነው እንጂ የወያኔ መንግሥት ውድቀትማ ቀጠሮም የሚያዝለትና የሚያስፈልገውም አይደለም።

ይልቁንስ እንዲህና እንዲያ ማለት ትተት ገደባችንና ልካችንን አውቀን ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ስናስተላልፍ መተካካቱ ተቆርጦ አዲስን ነገር ይበቅላል ነው። አርጌውን አልፎ አዲሱን ሲበቅልና ሲያብብ ደግሞ የነጻነት ችቦ ማየት ብቻ አይደለም በሚገባ እናጣጥማታለን። ይህ ማለት ግን እጅህንና እግርህን አጣምረህ ተቀመጥ እያልኩ አይደለም ያለሁትይ። እያለኩ ያለሁት ሰው ሲጨርስ እግዚአብሔር ይጀምራል! ነው።

- ሰው አቅሙን ሲያውቅ፥
- ሰው ገደቡንና ልኩን ሲረዳ፥
- ሰው ችሎታውን ግምት ውስጥ ሲያስገባ፥
- ሰው አቃተኝ ማለት ሲችል፥
- ሰው አሁንስ ረዳት እፈልጋለሁ ሌላው ቢቀር ራሴን መታደግ ማስመለጥ፣ የውስጥ ሰላሜን መጠበቅ አልቻልኩም! በማለት ነፍሱን አስጨንቆ ድምጹን፣ ህመሙን፣ ስብራቱንና ውድቀቱን ነፍስን ለፈጠረ ጌታ ስያሰማ፣ እጁንም ዘርግቶ ደካማነቱንና አቅመ ቢሲነቱን ሲያሳይ። የኃያላን ጉልበትና ቀንድ እንደ ጢስ የሚያበንና የሚሰበር፣ የአስጨናቂዎችን መታሰቢያ ፈጽሞ የሚያጠፋ፣ የትዕቢተኞችን ትዕቢት አስተንፍሶ እንደ አውሬ ሳር የሚያስግጥ አምላክ እደርሳለሁ ባለው ሰዓት ይደርሳል።

ሀያና ሰላሣ ዓመት አንቀጥቅጦ ለገዛም ቢሆን እግዚአብሔር "እንዴ! ትናንት በቴሌቪዥዮን መስኮት ይህን ያህል ፐርሰንት አድገት አስመዘገብን እያሉ መግለጫ ሲሰጡ አልነበሩም እንዴ ጠቅላይ ሚኒስትሩ?፣ ትናንት ይላሉ እንዴ እርስዎ አሁን አሁን አብረን ነበርን እያልክዎት" እስኪባል ድረስ መንግሥትነት ለሌላ አሳልፎ መስጠት ያውቅበታል። ይህ ሁሉ ከሰው አእምሮ በላይ የሆነውን አሰራር በምድራችን እውን የሚሆነው ግን እግዚአብሔር ለእሱ የተሰጠ ከደምነት ይልቅ ሰላምን ከጥላቻ ይልቅ ፍቅርንና አንድነትን አጥብቆ የሚሻ ልብ ያለው ትውልድ በምድሪትዋ ሲያገኝ ነው።

"እኔ አውቃለሁ፣ እናውቅላችኋለን" ማለት ግን ባርነትን የሚያጸና ዕንቅፋት ከመሆኑ በላይ ኃያላን መንግሥታት እርስ በርሳችን ስንናከስና ስንጨፋጨፍ ተሸከርካሪ ወንበራቸው ላይ ተቀምጠው መነጸራቸውን ዝቅ አድርገው (ደም መፋሰሳችን በደንብ ጥርት ብሎ እንዲታያቸው ማለት ነው) እንደሚመለከቱን ሁሉ የእግዚአብሔርም አሰራርና ማንነትም እንደሆነ ከዚህ የተለየ አይደለም። ዋናተኞች አንድ የሰመጠውን ሰው ለማውጣት ኃይሉን እስኪ ጨርስ ድረስ ጠብቀው ለመታደግ ጣልቃ እንደሚገቡ ይህንንም እርምጃ ለመውሰድ የሚገደዱት ያ ሰው በራሴ እተርፋለሁ ማለቱ ሲያቆም እንደሆነ ሁሉ ወደድንም ጠላንም የእግዚአብሔር አሰራርም እንዲሁ ነው። በተረፈ ገና አሁንም ራሴን አተርፋለሁ በሚል እሳቤ በኃይል መንፈራገጡ ያልተወና ያላቆመ እንደሆነ አድናለሁ ብሎ የገባ ሰውዬም ጨምሮ  መጥፋቱ ስለማይቀር ማንም የሚታደገው አይኖርም።

ውድ አንባቢ ሆይ! አሁንም ቢሆን የትርጉም መፋለስ/አለመግባባት ("ሚስ-አንደርስታንዲግ") እንዳይፈጠር እወዳለሁ። ኢትዮጵያውያን ከጠላታቸው ከወያኔ መንግሥት ለነጻነታቸው በሚያደርጉት ፍልምያ/ ግብግብ እግዚአብሔር በእንዲህ ያለ እሳት ጣልቃ መግባቱ/ቢገባ ያልታወቀች በራሪ ጥይት አግኝታው ይወደቃል/ሰለባ ሊሆን ስለሚችል ነው እያልኩ አይደለም ያለሁትይ። ከላይ ከፍ ስል ያስቀመጥኩት ምሳሌያዊ አነጋገሬን ለመረዳት እግዚአብሔር ለጌድዮን የተናገረውን ቃል ልብ ማለት ያስፈልጋል ይኸውም " እጂ አዳነኝ ብሎ እንዳይታበይብኝ እኔ ምድያምን በእጃቸው አሳልፌ አልሰጥም" እንዲል። ምን ነው? ቢሉ እግዚአብሔር በክብሩ ቀናኢ አምልክ ነውና አንድም ድሉን የሰጠህ እግዚአብሔር ሳለ አንተ በጉልበት ያደረግከው መስሎህ በልብህ ታብየህ በአንደበትህም ክፉ ተናግረህ ከመንግሥቱ እንዳትጎድል ነው።

እግዚአብሔርን ጠይቅ ስለግል ህይወትህ ስለ ሽንኩርት ጨው በርበሬህን ብቻ ሳይሆን ስለ ሀገርህ ስለ ትውልድህ አምርረህ በማልቀስ አለቅም! ፍረድልኝ! ፍትህን እሻለሁ! በማለት ጩክ። ኡ! ማለትህ የተባባረሩ መንግሥት ስብራትህ ባያውቅልህም ይልቁንስ በአንጻሩ "ኢትዮጵያውያን አበዱ" በማለት መግለጫ ለማውጣት ባይቀደምም እግዚአብሔር ደግሞ አጭቆና ነክሶ ከያዘህ ስሙ ከማይጠራ አውሬ መንጋጋ ያስጠለሃል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! በሰው ተስፋ ብትቆርጥም፣ ሁሉም በዓቅሙ ይሁዳ ቢሆንብህም ልብ የሚጣልበት በክፉ ቀን የሚታድግ እግዚአብሔር ታምነው። አሁንስ ማንን አምናለሁ ብለህ እጅህንና እግህን አጣምረህ ከተራብ ተኩላ ይልቅ የጠገበ ጅብ ይሻለኛል ብለህ ግራ ተግባተህ ለባርነት ራስህን አትስጥ። ሞትን አትመኝ!! በምንም ዓይነት መልኩ የጠገበ ጅብም ቢሆን አይሻልም! ጅብ ጅብ ነው። በምድሪትዋ ላይ የወጣ ጅብም እንደሆነ በልቶ የሚጠግብ አይደለምና ጠላትህን ግራ የሚያጋባ እንቆቅልሽህን ፈትቶ ዕረፍትንና መረጋጋትን የሚሰጥ አንድ አለ ስሙም ያለና የነበረ ይባላል ፊትህን ወደሱ መልስ።

አንድ ሆኖ ሳለ እንደ እስስት መልኩን እየለዋወጠና እየተተካካ ለመግዛት ወጥመድ ቢዘረጋ፣ ኃይሉም ከመቼው በበለጠ ቢያጠነክርና ቢታጠቅ የሰው ኃያል፣ ጀግናና ብርቱ የለውም። ሰማይና ምድር ቢጠየቁ፣ ተፈጥሮ ምስክርነትዋ ብትሰጥ፣ ፍጥረታት ቢናገሩ መልሳቸው እንደ እግዚአብሔር ያለ ኃያል፣ እንደ እግዚአብሔር ያለ ጀግና፣ እንደ እግዚአብሔር ያለ ብርቱ፣ እንደ እግዚአብሔር ያለ ፈጥሮ በፍትሕና በጽድቅ የሚገዛ ማንም የለም ነው። ኡ! በል ታግለህ የማትጥለው አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው። በተረፈ ግን የሰው አካኪ ዘራፍ ሰሜኑም ደቡቡም የእኔ ነው ማለት እስኪያዝ ድረስ ነው። የወገቡን  ጅማት የተነካ ዕለት ይቅር ሊፎክ ባርያውንም አቆላምጦ ቢጠራው ባሪያው በአቅሙ እጅግ ይጸየፈዋል። ያሰከረህን ያህል ጠላትህን አስክሮ የሚበቀልልህ እግዚአብሔርን ጥራ።

ውድ አንባቢ ሆይ! አሁንም በተደጋጋሚ ቀዳሚ ምርጫችንን እግዚብሔርን እናድርግ በእግዚአብሔር እንታመን ሲባል እንሞከረው እያልኩ አይደለም ያለሁትይ እግዚአብሔር ጸበል አይደለም የሚሞከረው። በፍጹም ልብህ ብትታመነው ይቻለዋል! ልመናችንን ሰምቶ ያደርጋል! በማለት አንዷት ቀንም ብትሆን ከሊቅ እስከ ደቂቅ በርህን ዘግተህ ወላጆች በለጋ ዕድሜያቸው በአረመኔው መንግሥት ጥይት የተቁሉ የልጆቻችሁን ስእል፣ ያላአሳዳጊ የተበናችሁ ቤተሰብ የወላጅ ስእል፣ አሁንም ያለ ምክንያት በየማጎሪያ ቤቱ በእስር የሚሰቃዩ አባት ልጅ እናት እህት ሊሆኑ ይችላሉ ክሳቸውን ይዘን ተመልከት በማለት በፊቱ እንድንወድቅ እግዚአብሔር ቢረዳንና ዕድሉ ቢሰጠን የንጉሡን ደብዳቤ ያነበበ ኃያል አምላክ የኢትዮጵያውያን ግፍና አረሮ አይቶና ሰምቶ ተነስ! ከዚህ በኃላ ተራው የእኔ ነው የማይልበት ያዘነውን ሕዝብ የማያጽናናበት በደም ለሰከረች ምድርም ቢሆን በቃሽ የማይልበት ምክንያት የለውም። ከልብ ሳይሆን በአንደበቱ ሀገሬ፣ ሕዝቤ፣ ባይ ወገንም እንደሆነ በእኔና እናንተን ዓይን ላይ ብዥታ መፍጠራቸውን እንደተጠበቀ ሆኖ

በእግዚአብሔር መንጽር ሲታዩ ግን ማስካቸውን አውልቆ እውነታኛ ማንነታቸው ለመናገር ደቂቃም አይፈጅበትምና ትፈርድባቸውና ትወድቅባቸውም ዘንድ ክብርህ ስለሆነ በእጅህ አሳልፎ ይሰጥሃል።

እግዚአብሔር ግብዝነት በተሞላበት እምነት ሳይሆን በንጹህ ልብ በኢትዮጵያውያን ላይ ቀዳሚ ስፍራ ስይዝ በፖለቲካችን ላይ "እኛ እናውቃለን" "እናውቅላችኋለን" የሚለውን መፎክርን ትተን የበላይ እግዚአብሔር ሲሆን ያለፈ አልፈዋል ከእንግዲህ ወዲህ ግን ማንም በምድሪትዋ ላይ አይፈራረቅባትም። ይሁዳ አልፎ ሲያበቃ ይሁዳ አይተካም። ትግልህ ኡ! ማለትህ አረመኔው የኢህአዴግ መንግሥት ለመጣል ብቻም ሳይሆን ከዛ በኋም ለሚመም እግዚአብሔር ኃላፊነቱ ይወስዳል። የዚህ ውጤት ደግሞ ምድሪትዋ መልካምን ዘር ታበቅላለች ትውልድዋም ከምትሰጠው ዘር የተነሳ በልቶና ጠግቦ ያድራል። ካስፈለገም ለሱዳንና ለኬንያ እንዲሁም ለሌሎች የአፍሪካ ከተሞች እየሸጠን ዕዳችንን ከፍለን ኢኮኖሚያችንን በማሻሻል ባርነትን ወድያ በማለት በዓለም የነበረን ገጽታ ቀይረን በየትኛውም ስፍራ እኩል ከሰው ልጅ ጋር እንቆማለን (2ኛነገ. 4፥7) ።

ምርጫዎ እግዚአብሔርን ያድርጉ!! ምርጫው እግዚአብሔር ባደረገ ትውልድ ላይ ማንም ቁጣው አያበርድበትም። ቁጣው በራሱ ላይ ይሆናል እንጂ አሞክራትምም። እንግዲህ በኢትዮጵያ ምድር የሚካሄደውን ምርጫ በሁለት ወገኖች ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርም የዚህ ምርጫ አንድ አካል ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! እግዚአብሔርን ስትመርጥ ዛሬም እንደለመደው ከውጭም ከጥልቁም አማካሪዎችን ሰብስቦ የጥይት ድምጽ ሳያሰማ በተካነ ሳይንሳዊ ሌብነት ምርጫውን ማሸነፍ ይቻለው ዘንድ ሌተቀን ከሚተጋ መንግሥትም ሆነ በሕዝብና በሀገር ስም ሰው የማያውቀውን ያላወቅውን መራራ አጥፊና ክፉ ምኞት ደብቆ የህዝብ ያይደለ የህዝብ በሚል ሽፋን የተለበጠ አጀንዳ ይዞ የሚወጣም በናፍቆት የሚጠባበቅዋትን ቀን ሳትደርስ ምክራቸው ለንፋስ አጀንዳቸውንም ለእሳት ሰዎቹንም ቦታ ቦታቸውን አስይዞና አሸጋሽጎ እንደ ልቡ የሆኑትን አንተም ያለ ጸጸት ደስ ተሰኝተህባቸው ሀገርም ሀገራችን ናት ህዝብም ህዝባችን ነው ተባብለህ በአንድነት በመተባበር በመዋደድና በመተሳሰብ እጅ ለእጅ ተያይዘህ "ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!" የሚለውን ቅኔ እየዘመርክና እየተቀባበል እንደማንኛውም ዜጋ ለተፈጠርክበት ዓላማ መኖር ትችል ዘንድ ምርጫህ እግዚአብሔር ይሁን!!

ስለ ሁሉም የእስራኤል ቅዱስ እግዚአብሔር ዓይነ ልቦናችንን ያብራ!!

ዲ/ን ሙሉጌታ ወልደገብርኤል
yetdgnayalehe@gmail.com